4127 Redwood
Oakland, CA 94610
(510) 530-3681

# አስደሳች መንፈሳዊ ዜና

*“መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩናቸው ተብሎ እንደተጻፈ…”* ሮሜ 10፡15።

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !

## ዜና ተዋሕዶ ዓለም አቀፍ የራዲዮ ድምጽ አገልግሎት

ለኦርቶዶክሳውያን ምዕመናን በሙሉ፡-

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዜና ተዋህዶ በመባል የሚታወቀውን ዓለም አቀፍ የራዲዮ አገልግሎት ድምጽ በ15260 kHz ወይም በ19 ሜትር ባንድ በየሳምንቱ ሰኞ በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ፤በቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ከሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. (July 2nd, 2007) ጀምሮ የስብከተ ወንጌልና ልዩ ልዩ የመንፈሳዊ አገልግሎት ስርጭት መጀመሩን በደስታ ያበስራል። በተጨማሪም የቅዱስ ሲኖዶሱ ስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ይህንኑ መንፈሳዊ አገልግሎት ለመላው ዓለም አድማጮች ለማዳረስ ባወጣው ዕቅድ መሠረት የቅዱስ ሲኖዶሱን ድህረ ገፅ WWW.EOTCHOLYSYNOD.ORG በመጎብኘት ከበረከቱ ተካፋይ እንድትሆኑና ለሌሎችም እንድታሳውቁ በልዑል እግዚአብሔር ስም በትህትና ይጠይቃል።

ሰላመ እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን!

ሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ